# ትልቅ ሥጋት አድሮብኛል

ደምለው አልማው

የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል መሪ የለውም:: እራሱም ወደእዚህ ትግል ሲገባ በተመከረበት: በተጠና: ዝግጅት በተደረገበት: ታክቲክና ስትራቴጂ በተነደፈበት ሁኔታ አልነበረም:: በቁጣ: በንዴት: በብስጭት እና በብሶት ተነሳስቶ ነው ትግል ውስጥ የገባው:: ለምንእንዲህ ሆነ ብሎ እራስን መጠየቅ ግድ ይላል:: እኔ በበኩሌ እራሴን ጠይቄአለሁ:: የእገኘሁት መልስ የሚያገለግለው ለራሴ ብቻ የሚሆን ቢሆንም እራሴን ጠይቄ ለእራሴ ባገኘሁት ምላሽ ትልቅ ሥጋት አድሮብኛል::

የአንድ ነጠላ ግለሰብ ሥጋት ተፈጠረ አልተፈጠረ ላያስጨንቅ ይችላል:: ግን ሌሎች እንደኔ ዓይነቱ ጭንቀታም ሚሊዮን ሕዝብ ቢኖርስ? በእርግጥ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል:: ዋናው ነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ተስፋ በማድረግ 25ዓመታት ቆይቶአል:: ተቃዋሚዎች ግን እያደር እየጠነከሩ ከመሄድ ይልቅ እያደር እየላሉ: እየተበታተኑ: እየሳሱ እየደከሙ: ሞራላቸው እየደበዘዘ: ቀለማቸው እየወየበ: መንፈሳቸው እየደከመ ሄደ:: በእራስ ድርጅት ውስጥ የተለያየ ሃሳብ አስተናግዶ ዴሞክራሲን ተለማምዶ የድርጅት ጥንካሬን ያሳያሉ ተብሎ እምነት ቢጣልባቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ እምነት እንዲሰበር አድርገዋል:: እንደ ልጆች ጨዋታ አንዴ ሲከቡ : አንድ ጊዜ ሲንዱ: አንዴ ሲመሠርቱ: ሌላ ጊዜ ሲያፈርሱ ተስተውለዋል:: በማያለያይ ርዕዮ-ተዓለም ተለያይተው: በማያጣላ ተጣልተው: በማያቀያይም ተቀያይመው: ሃያ አምስት ዓመታትን አስቆጥረዋል:: ዛሬም ያው ናቸው::

በርካታ የፖለቲካ ሰዎችና ድርጅቶች የፕሪንሲፕል ጉድለት: የዲሲፕሊን ችግር ያለባቸው ናቸው:: ለምሳሌ በድርጊታቸው ማስረዳት ይቻላል:: በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ልዩነቶቻቸውን ማዛመድ አልቻሉም:: የገመድ ጉተታ ስታይል እንደያዙ አሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነዚህ ፍሬ ስለማግኘቱ ጥርጣሬ ውስጥ ወደቀና እራሱ ተንደርድሮ ሊያመጽ ቻለ::እነሱ ተቃዋሚዎች መሥራት ያለባቸው የቤት ሥራ ሕዝብ ሲሠራላቸው እነሱ የሚቀጥለውን: ትግሉ እንዴት መራመድ እንደሚገባ: በጥናት የተደገፈ የተቃውሞ ፕላትፎርም ማቅረብ ተስኖአቸዋል:: ይልቁን ሕዝብ የሞተውን ያህል ሞቶ እነሱ መንገስ የሚችሉበትን መንገድ ነው ያሳሰባቸው:: እናም በአሁኑ ሰዓት ስለትግል: በትግል ውስጥ ስለሚዋደቁ: ስለሚቆስሉ ስለሚሞቱ: ስለሚታፈሱ ሕዝቦች ያሳሰባቸው አይመስሉም:: ምክንያቱም እንቅስቃሴአቸው በሙሉ የመንገሻ እንቅስቃሴ ሆኖ ስለሚታይ::

በሌላ ጎን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የሚል ስያሜ ወስደው ለወያኔ ተሳላሚ በመሆን እራሳቸውን በወያኔ እርጥባን ማስተዳደርን ዘመናዊነት አድርገው የያዙ አስነዋሪዎችና አስደፋሪዎች እራሳቸውን አስንቀው የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲናቅ በር ከፍተዋል:: ለወያኔ የሚያገለግሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ሎሌዎች በርካታ ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነዚህ ላይ የማያዳግም እርምጃ ባለመውሰዱ ተሳላሚ ሎሌዎቹ ለበርካታ ወጣቶች መጥፎ አረአያ በመሆን ትውልዱን መርዘውታል:: አሁንም አልተኙም:: ዛሬም በኢትዮጵያ ሕዝብ ደምና ሕይወት እየነገዱ ናቸው:: እነዚህን በግል ደረጃ ሳይቀር ስማቸውን መንቀስ: ድርጅታቸውን መጥቀስ ይቻላል:: በመሆኑም እውነተኛና ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት እንዳይፈጠር እንደ ነቀዝ ውስጥ ውስጡን በመሄድ አደገኛ ሚና ተጫውተዋል:: ነገ የምንፋረዳቸው ይሆናል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በምናልባት ወያኔ በእራሱ ታርሞ ወይም ተገስጾ ቀናውን መንገድ ያይ ይሆናል ተብሎ በተሰጠው

ሩብ ምዕተ-ዓመት ጊዜ ውስጥ ይለወጥ ይሆናል ተብሎ በተስፋም: በጥርጣሬም ቢጠብቀውም ወያኔ በባለጌ አስተሳሰብ ትዕግስትን እንደፍራቻ: ዝምታን እንደአላዋቂ በመቁጠር የማይደፈረውን ሁሉ ተዳፍረው አረፉ:: ለእያንዳንዱ የህወኃት ባለሥልጣን እና ጄኔራል የአገርንና የሕዝብን ሀብት እንደግል ንብረታቸው አይተው ከመቆንጠር ወደ መመዝበር: ከመመዝበር ጨርሶ ወደግል ሀብትና ንብረት የማዛወር ድፍረታቸውን በማን አለብኝነት በአደባባይ አረጋገጡ :: አንድ የመንግስት ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆነ ደመወዝተኛ ፈጽሞ በመቶ ዓመት ሊያጠራቅም የማይችለውን ገንዘብ ባለቤት በመሆን ሚኒስትር ኢንቨስተር: ጄኔራል ሚሊየነር ሆነው እንደተገኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትክክል ያውቃል:: በዚህም አገር ደኸየች::

ልማት ስለሚባለው ነገር አንድ ነገር ልጠቁም:: እንደ መንግስት ዕቃ ግዢ ሲያዙ እነሱ ራሳቸው ሲሆኑ: እንደ ነጋዴ የሽያጭ ዕቃ አቅራቢም የራሳቸው ድርጅት ነው:: እንደመንግስት የመንገድ ኮንስትራክሽን ጨረታ ያወጡና እንደ የግል ኮንትራክተር ጨረታውን የሚያሸንፉት እና ሥራውን የሚወስዱት እራሳቸው ናቸው:: እንደ መንግስት የውጭ እንቨስተር ይጋብዙና ሕጉን ተንተርሰው ከውጭ ኢንቨስተር ጋራ ሽርክና ማህበር የሚመሰርቱትም እራሳቸው ናቸው:: በዚህ ድራማ እና ትዕይንት ውስጥ ቤተሰቦች: ልጆች: አማቾች: አበ-ልጆች: የአጎትማማቾች ልጆች: የእክስትማማች ልጆች እናም ቀለም ያሳምራል እየተባለ ጥቂት ታማኝ አጋፋሪዎችን እያቀማመሱ ሥራውን የሚቆጣጠሩት እራሳቸው ወያኔዎች ናቸው:: እስቲ በኢትዮጵያ ከግል ኮሌጆች ውስጥ ባለድርሻ ያልሆነ ባለስልጣን አለ? ሊኖር ከቻለ 99 ፐርሰንቱ ውስጥ ወያኔ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የወያኔ አክሲዮን ባለቤትነት ያውም የአንበሳ ድርሻው አለበት::

አዲስ አበባ ከተማ ያለውን ፎቅ መቁጠር ይቻላል:: ያለውን የንግድ ድርጅት መዘርዘር ይቻላል:: ስለዚህ ወያኔ ባለሥልጣን ነው:: ባለሀብት ነው:: ኢንቨስተር ነው:: በድፍኑ የኢኮኖሚ ፓወሩንም ሆነ የፖለቲካ ኃይሉን በእነሱ መዳፍ ካስገቡ ቆየ:: አሁን ደግሞ ድፍረቱ እየባሰ ስለመጣ : የትግራይን ሪፐብሊክ ለመመስረት አገርትዋን ሸጦ መጨረስ: በዕዳ አስይዞ ከማትወጣበት ማጥ ውስጥ ከትቶ እራስን ወደ ትግራይ ከልሎ በተባበሩት መንግስታት አሳውጀው ሉዓላዊ አገር ሆነው እራስን ለመከላከል አገር የመዝረፍ ተግባር ውስጥ ገቡ ::

ይህንን ውስጥ ለውስጥ ሲሠሩ የኖሩት ድብቅ አጀንዳ እያፈተለከ መውጣት ሲጀምር ብረት ማንሳት ጀመሩ:: ሰው መግደልን የአስተዳደር ሥራ አደረጉት::እነሱን የነካ የማርያም ጠላት እንዲሆን አደረጉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ማየትና መስማት ስላልቻለ በንዴት ወደ ትግሉ ገባ:: እዚህ ላይ አክቲቪስቶች የሕዝብን ንቅናቄ ለማጋጋል ሰፊ እና ጥልቅ ሚና ተጫውቱ:: ጋዜጠኞች የሚነበብ ታሪክ መሥራት ጀመሩ::

ይሁን እንጂ የአክቲቪስቶችና የሲቪል ተቋዋሞች ጥረት የራሱ የሆነ እገዛ እንዳለው ባይካድም ለሕዝብ ስልትና ስትራቴጂ ሆኖ የሕዝብን ትግል ደረጃ በደረጃ ድል በድል ድል በድል አድርጎ አላራመደውም:: የዐመጽ መቀጣጠልና እንደ ሰደድ እሳት መስፋፋት እንደ ድንቅ ሂደት እንጂ እንደ ድል ማየት ስህተት ይሆናል::

ወያኔ ግን ስልታዊ አካሄድ በመሄድ ላይ ነው:: በያንዳንዱ ጭቅጭቅ የተረታ: የተሸነፈ: የደከመ ያስመስል ይሆናል እንጂ አይደለም:: የማዘናጊያ ሥራዎች በብዛት እየተሰሩ ናቸው:: ትውልዱን በጅምላ እየጨረሱ ናቸው:: ትላንት ዐመጹ ሲቀጣጠል የተቃውሞው ሞተር የሆነ ወጣት ዛሬ የት እንዳለ የሚያውቀው ወያኔ ብቻ ነው:: በዚህ ዓይነትና ሁኔታ ከቀጠለ መጨረሻው የከፋ ሀዘን ይሆናል:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይተካ ትልቅ ኪሣራ ጭምር ሳይሆን ዘለዓለማዊ ውርደትም እንደሚሆን ነው:: ጉዳዮችን ሰክኖ ማየት ያስፈልጋል:: አርቆ ማስተዋልን ይጠይቃል:: በደቦ መሄድ: በዘመቻ መገስገስ ሕግና ሥርዓት መሪና መርሆ ከሌለ በአሳዛኝ ሁኔታ ሕዝብ ይበደላል::

በተለይ አንኩዋር አንኩዋር የሆኑ በተለይም ጎላ ጎላ ያለ ድምጽ ያላቸው የኦሮሞ ወጣት አክቲቪስቶች ሦስት መቶ ስልሳ

ድግሪ ዘረው ማሰብ አለባቸው:: የራሳቸውን ስሜት ብቻ ሳይሆን የሕዝብን ፍላጎት ተረጋግቶ መስማት: በጥሞና መመረመር: የታለፈውን የትግል ወራት መገመገም ግድ ይላል:: አሁን እነደሚታየው ሁሉም ሩጫ ላይ ነው:: ቆሞ የሚያይ እየጠፋ ነው:: ቁጭ ብሎ ነገሮችን የሚመረምር ያለ አይመስለኝም:: በሩጫ ሰዓት ለሩጫ የሚሆን ነገር ለመስማት መፍቀድ ትክክል አይደለም:: ሲሰሙት የሚያስደስት ወይም መስማት የፈለጉትን ብቻ መርጦ መስማት በሕዝብ ትግል ውስጥ ቦታ የለውም:: ምናልባትም ትግሉ በአሉታዊ ከተደመደመ ያስጠይቃል:: ጸጸቱም ከባድ ነው ::ለሽከምም የሚከብድ ነው:: በዚህ ሩጫ ውስጥ ከልምድ እጥረት ከግንዛቤ ጨቅላነት ከወጣትነት ስሜት እየተነሱ በራስ ስሜት ብቻ መመራት ተገቢ አይደለም::

የኢትዮጵያ የትግል መሪ ይጠይቃል:: መሪ የሌለው ትግል የትም አይደርስም:: ሕዝብ ትግሉን ጀመረ እንጂ ሕዝብ የትግሉ ባለቤት ሆነ እንጂ መሪ ነኝ አላለም:: መሪ እኮ መሪ ነው:: ሕዝብም ሕዝብ ነው:: መሪ አለ ከተባለ ዕቅድ አለ:: ስትራቴጂ አለ:: ታክቲክ አለ:: ስልት: መርሐ ግብር አለ:: መመሪያ አለ:: እያንዳንዱ ሕዝብ እንደ የችሎታው መሥራት ያለበትን ሥራ ሠራ ማለት ነው:: አንድ የጦ. ሠራዊት በውትድርና ስለ ሰለጠነ በውጊያ ዕውቀት ስላገኘ የውጊያ መሣሪያ ስላነገተ ብቻ በጦ. ሜዳ ያለ መሪ ጦርነቱን አካሂዶ አሸናፊ ይሆናል ብሎ መገመት ትልቅ ስህተት ነው:: ምናልባት የከፋ ስህተት::

ስለዚህ ሕዝብ መሪ እየጠየቀ ነው:: ሕዝብ የሚያዋጣ ስልት እየፈለገ ነው:: አቅብሉን እባካችሁ እያለ ነው:: ትውልዱ ከነጉልበቱ ከነኃይሉ ወያኔ እጅ እየገባ አስከፊ ሕይወት ውስጥ ገብቶአል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያስተባብር እንደሰንሰለት አያይዞ የሚያታግል የተማሩ ብቻ ሳይሆን በውጊያ ውስጥ ያለፉ ልምድ ያላቸው ሰዎች የተሳተፉበት አንድ የሆነ ማዕከል ወይም የተፈለገውን ስም ይሰጠው ብቻ አሁን ያስፈልጋል::

እራስንም ሕዝብንም ማደራጀት ያስፈልጋል:: እኔ ይህንን አጭር መልእክት ከመጻፌ በፊት በራስ ተነሳሽነት የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ሰዎችን በማንኛውም ዘመናዊ መገናኛ ለማግኘት ጥሬ አልተሳካልኝም:: ከአቶ አባንግ ሜቶ በስተቀረ ሄሎ ብሎ ስልኩን ያነሳልኝ ሰው የለም:: የኔ ስልክ ግድ ለምን አልተነሳም ማለቴ አይደለም:: በጦር ሜዳ ንቁ ጆሮ: የተረጋጋ አስተዋይ ልብ እንደሚያስፈልግ ስለማውቅ ነው:: ጊዜ ወስዶ በረጅሙ ተንፍሶ እራስን አዝናንቶ ማሰብን ይጠይቃል:: ዘወትር እንደሚዜ እና እንደሙሽራ ዓይነት ግርግር ብቻ: ሕዝብን ወደ ተሳሳተ ጎዳና ይወስዳል::

ይህን ይህን ሳይ ክፉ ሰው ቶሎ አይሞትም አፈር ልሶ ይነሳል እንዲሉ ዓይነት የወያኔን ተፈጥሮአዊ ባህርይ ስመለከት እያለቁ ያሉትን ወጣቶች ስሰማ ሳይ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ጉዳይ እንደ አንድ ተወላጅ ትልቅ ሥጋት ፈጥሮብኛል!